አዲስ ትምህርት-ቤት ሲመርጡ ከግምት ማስገባት ያለብዎ ጥያቄዎች

አዲስ ትምህርት ቤት መምረጥ አስደሳች፣ አስደናቂ እና አንዳንድ ጊዜም ከባድ ስሜት የሚፈጥር ሂደት ሊሆን ይችላል። ይህ ደግሞ ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ቤተሰቦች ይበልጥ እውነት ሊሆን ይችላል፣ ምክንያቱም ስለ ፕሮግራሚንግ፣ ድጋፎች፣ የትምህርት-ቤት-አቀፍ ስርዓቶች እና ስለ ሌሎች ጉዳዮች ሌሎች ተጨማሪ ጥያቄዎች ሊኖራቸው ይችላል። ልጃችሁ የሚማርባቸው ትምህርት ቤቶች በሚመርጡበት ጊዜ ምን መጠየቅ እንዳለብዎ ለመወሰን ከታች የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች ይጠቀሙ!

የት-ምህርት-ቤት ፖሊሲዎች እና ባህል

- [ ] የተሳትፎ ፖሊሲዎ ምንድነው?
- [ ] ትምህርት-ቤትዎ ከባህሪይ እገዛዎች እና ዲሲፕሊን ጋር በተያያዘ የሚከተለው አሰራር እንዴት ያለ ነው? ከዚህ ቀደም ተጨማሪ የባህሪይ እገዛዎች ለሚሹ ተማሪዎች ያደረጋቹት ነገር ምንድነው?
- [ ] ከቤተሰቦች ጋር እንዴት ነው የምትሰሩት? PTO ወይም የወላጅ አማካሪ ኮሚቴ አላቹ?
- [ ] ትምህርት-ቤትዎ በቅርቡ ያጋጠሙት ትልልቅ ተግዳሮቶች ምንምን ናቸው? እንዴት ነበር እነዚህን ተግዳሮቶች ያለፋችዋቸው?
- [ ] ቀዳሚ እና ተከታይ እንክብካቤ ትሰጣላቹ? እንዴት ነው የማመለክተው? በቤት ውስጥ ነው ወይስ በኮንትራክተር አማካኝነት ነው የሚሰጡት? How do you ensure እነዚህ አገልግሎቶች ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ተደራሽ መሆናቸውን እንዴት ነው የምታረጋግጡት?
- [ ] ምንምን ተጨማሪ ትምህርቶችን ታቀርባላቹ? ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ተደራሽ መሆናቸውን እንዴት ነው የምታረጋግጡት?

አካዳሚክስ እና ስርአተ-ትምህርት

- [ ] ትምህርት ሞዴላችሁ ምንድነው? ተማሪየ ስለ ሚማረው ነገር እንዴት ነው የበለጠ ማወቅ የምችለው?
- [ ] ምንምን አማራጮች ወይም ልዩ ዕድሎች ታቀርባላቹ? እነዚህ እንዴት ነው ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ተደራሽ የሚሆኑት?
- [ ] የእኔ ተማሪ ስንት የቤት-ስራ ነው መጠበቅ ያለበት? አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች እንዴት ነው በቤት-ስራ የሚታገዙት?
- [ ] ስርአተ-ትምህርታቹ እንዴት ነው ለልዩ ትምህርት ተማሪዎች ተሻሽሎ የሚቀርበው?
- [ ] የተማሪ እድገትን እንዴት ነው የምትከታተሉት? ምን አይነት ምዘና ነው የምትጠቀሙት (MAP, ANET, I-Ready, ወዘተ) እንዲሁም በየስንት ጊዜው ነው የሚሰጡት?
- [ ] ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ምን ዓይነት ቴክኖሎጂ ይጠቀማሉ? ቴክኖሎጂን ወደ ቤት ማምጣት ይችላሉ?
- [ ] ማንኛውንም የተዋሃዱ የመማሪያ ፕሮግራሞችን (ሌክሲያ፣ አይ-ዝግጁ፣ ST ሂሳብ፣ ወዘተ) ይጠቀማሉ? እነዚህ ፕሮግራሞች በክፍል ውስጥ እንዴት ጥቅም ላይ ይውላሉ?

የት-ምህርት-ቤት ስታፍ

- [ ] የሙሉ ጊዜ ነርስ ሰራተኛ አላቹ? ካልሆነ፣ መድሀኒት ያላቸው ወይም ሌላ የሕክምና ፍላጎቶች ያላቸው ተማሪዎችን ለመርዳት ምን አሰራር ትከተላላችሁ?
- [ ] አማካይ በአንድ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎቻቹ ብዛት ስንት ነው? ለተማሪየ የትምህርት ደረጃ የሚመደቡ ሰራተኞች ብዛታቸው ስንት ነው? ይህ ለልዩ ትምህርት ተማሪዎች የተለየ ነው?
- [ ] ማነው ለልዩ ትምህርት ተማሪዎች የባህሪይ እገዛ አገልግሎቶችን የምያቀርበው (የምክር አገልግሎት ሰጪ፣ማህበራዊ ሰራተኛ፣ወዘተ)? እነዚህ ሰራተኞች ብዛታቸው ስንት ነው?
- [ ] የእኔ ተማሪ የንግግር ቴራፒ/የሙያ ቴራፒ/አካላዊ ቴራፒ/ወዘተ ይፈልጋል። ከሰራተኞችዎ ውስጥ ማን ነው እነዚህን አገልግሎቶች የምያቀርበው?
- [ ] ከተማሪየ ጋር ሊሰሩ የሚችሉ የባህሪይ ስፔሻሊስት፣ የትምህርት-ቤት ስነልቦና ባለሙያ፣ ወይም ሌሎች ስፔሻሊስቶች አሏቹ?

ተጨማሪ እገዛዎች

- ☐ ማስጠናት፣ የጥናት አዳራሽ፣ ወይም ሌሎች ተጨማሪ አካዳምያዊ እገዛዎችን ትሰጣላችሁ? የእኔ ተማሪ እንዴት ነው እነዚህን እገዛዎች የሚጠቀመው?
- ☐ ምን አይነት የአካዳምያዊ ፕሮግራም ኢንተርቨንሽኖችን ነው የሚጠቀሙት (Read 180, Seeing Stars, ወዘተ)? ተማሪዎች እንዴት ነው የኢንተርቨንሽን ፕሮግራሞች የሚመደቡላቸው?
- ☐ የእኔ ተማሪ ተጨማሪ ወይም የተለየ እገዛ ያስፈልገዋል ብየ ብጠረጥር ምንድነው ማድረግ ያለብኝ?
- ☐ ምንምን ተጨማሪ እገዛዎችን ታቀርባላችሁ? እነዚህ ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ተደራሽ መሆናቸውን እንዴት ነው የምታረጋግጡት?
- ☐ እንዴት ነው ከቤተሰቦች ጋር የምትግባቡት? ከተማሪየ አስተማሪ በየስንት ጊዜው ነው መገናኘት ያለብኝ?

ልዩትምህርት

- ☐ የልዩ ትምህርት አተገባበር ሀላፊ ማነው (የልዩ ትምህርት አስተባባሪ፣ የ LEA ተወካይ፣ ወዘተ)? እንዴት ነው ላገኛቸው የምችለው?
- ☐ እንዴት ነው የልጄ ኬዝ መሪ የሚመደበው? በየስንት ጊዜው ነው እነሱን ለማግኘት መጠበቅ ያለብኝ?
- ☐ የልጄን IEP/504እቅድ በተመለከተ የምያሳስበኝ ጉዳይ ካለ ማንን ነው ማናገር ያለብኝ?
- ☐ ከዚህ በፊት የልጄ አይነት የአካል ጉዳት/ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን እንዴት ነበር ስትረዷቸው የነበራቹት?
- ☐ በአሁኑ ጊዜ አካታች ትምህርት/መማሪያ ክፍል ውስጥ የሚሰጡ ትምህርቶች፣ የሪሶርሶች ክፍል/ከመማሪያ ክፍል ውጪ ትምህርት፣ወይምየልዩ ትምህርት ተማሪዎች ትምህርት በተመለከተ ምን አማራጮች አሏቹ?

ሽግግሮች

- ☐ ልጄ አካል ጉዳተኛ ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ነው ትምህርት እየጀመረ ያለው። የምያስፈልገው እገዛ ማግኘቱን እንዴት ነው የማረጋግጠው?
- ☐ ልጄ ከመለስተኛ ትምህርት-ቤት/ወደ መለስተኛ ሃይ ስኩል/ወዘተ ነው እየተሸጋገረ ያለው።ምን አይነት ለውጦችን እንጠብቅ?
- ☐ ልጄ ሃይ ስኩል በመጀመር ላይ ነው። በዲፕሎማ ትራክ እና በ IEP ማጠናቀቂያ ሰርትፊኬት ትራክ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? ከእሱ ጋር የበለጠ የሚጣጣመው ትራክ የትኛው እንደሆነ እንዴት ነው የምንወስነው?
- ☐ የሙያ ስልጠና፣ የሰርትፊኬሽን ኮርሶች (ኮስሚቶሎጂ፣ወዘተ)፣ የ AP/IB ክላሶች፣ ወይም ድርብ ተሳትፎ ታቀርባላቹ? እነዚህ ዕድሎች እንዴት ነው ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ተደራሽ የሚሆኑት?
- ☐ አካላ ጉዳተኛ ተማሪዎችን ለኮሌጅ እና/ወይም ለድህረ-ምረቃ ስራ በማዘጋጀት ረገድ እንዴት ነው እርዳታ የምታቀርቡት?
- ☐ ልጄ ከግል ትምህርት-ቤት ወደ ህዝብ ትምህርት-ቤት ወይም ከህዝብ ትምህርት-ቤት ወደ ግል ትምህርት-ቤት ነው እየቀየረ ያለው። የልዩ ትምህርት እገዛዎች ልዩነታቸው ምን ይመስላል?

ተጨማሪ ጥያቄዎች/ማስታወሻዎች

ዲሲ ውስጥ ስለ ሚሰጠው ልዩ ትምህርት ተጨማሪ ጥያቄ አሎት? ለተጨማሪ እገዛ የዲሲ ልዩ ትምህርት ማእከልን ያናግሩ!